# STREAM Disinfectant Generator (ፀረ-ተባይ ማመንጫ)

# የተጠቃሚ መመሪያ



AQUA RESEARCH

<u>እርምጃ 1 - የጨው ሙመሙት ያዘጋጁ</u>

ፀረ-ተባይ ሙመሙት ማመንጨት ለማስጀመር በመጀመሪያ የጨው ሙመቱ መዘጋጀት አለበት። የሚከተሉትን ቁሳቁሶች ያዘጋጁ፡-

– ጨው
– ቀዝቃዛ፣ንጹህ ውሃ
– ለመደባለቅ የእንጨት ማማሰያ
– 2 x 20 ሊትር ባልዲዎች

20 ሊትር የጨው ሙመሙት ለማዘጋጀት፣ ከታች ያሉትን ደረጃዎች (ቅድም ተከተሎች) ይከተሉ የተለያዩ መጠኖችን ለመቀላቀል ከዚህ በታች ያለውን ሰንጠረዥ ይመልከቱ።

1 ባልዲው ውስጥ 20 ሊትር ውሃ ይሙሉ።
2 300 ግራም ጨው ይጨምሩ።
3 ጨው እስኪሟሟ ድረስ ያማስሉ።
ማስታወሻ፡- የተለያየ የጨው ሙመሙት መጠን ዝግጅት ላይ ተጨማሪ መመሪያ ለማግኘት ከዚህ በታች ያለውን ሰንጠረዥ ይመልከቱ።

| መጠን፡- የውሃ ሊትር (ጋሎን) | መጠን፡- የጨው ግራም (oz) | የጨው ሙመሙት መጠን |
|---|---|---|
| 1 (0.26) | 15 (0.4) | 1 ሊ |
| 5 (1.3) | 75 (2) | 5 ሊ |
| 10 (2.6) | 150 (4) | 10 ሊ |
| 20 (5.3) | 300 (8) | 20 ሊ |

<u>እርምጃ 2 - ማዋቀር</u>

1 የ STREAM መሰሪያ መያዣውን ይክፈቱ።
2 ከኃይል ምንጭ ጋር ያገናኙ።
3 ቀለም አልባ የፕላስቲክ ቱቦዎቹን ከመጠቅለያቸው ያውጡ።
4 ትንሹን ቱቦ ከትልቁ ቱቦ ጋር ከተገናኘበት ቦታ ላይ ያላቅቁት።
* ጥንቃቄ፡- ትንንሽ የቱቦ ድጋፎቹ ከትቦዎቹ እንዳይለቁ ያድርጉ።
5 የጨው ሙመሙት መምጠጫ ማጥለያውን ከትንሹ ቱቦ ጋር ያያይዙ።
6 ትንሹን ቱቦ በደረጃ 1 የተሰራው የጨው ሙመሙት ባልዲ ውስጥ ያድርጉት።
7 ትልቁን ቱቦ ሁለተኛው ባልዲ ውስጥ ያድርጉት።
* የፀረ-ተባይ ባልዲው መጠን ከጨው ሙመሙት ባልዲው ጋር ተመሳሳይ ወይም የሚበልጥ መሆኑን ያረጋግጡ።

<u>እርምጃ 3 - ማስጀመር</u>

1 የማስጀመሪያ አዝራሩን በመጫን መሳሪያውን ያብሩ። ON/OFF (የማብሪያ/ማጥፊያው) አዝራር ዙሪያ አረንጓዴ የLED መብራት መታየት አለበት።
2 መሳሪያው፣ ከጨው ሙመቱ ፈሳሽ በማውጣት ፀረ ተባይ ማመንጨት ይጀምራል።
3 የሚመረተው ፀረ-ተባይ በቋሚነት በአንድ ሚሊዮን 5,000 ክፍሎች እንዲሆን ፓምፑ ፍጥነቱን ያስተካክላል (ppm) mg/L።
4 ስህተት ከተገኘ ON/OFF አዝራር ዙሪያ የበራውን የLED መብራት በመመልከት ተጓዳኙን መንስኤ እና መፍትሄ ይፈልጉ።
5 ON/OFF አዝራር ይጫኑ እና እንደገና ያስጀምሩ።
6 የሚፈልጉትን ያህል የፀረ-ተባይ መጠን ካመነጩ በኋላ መሳሪያውን ለማቆም ON/OFF ቁልፍን ይጫኑ ወይም እንደ አማራጭ የጨው ሙመቱ አልቆ ባዶ በሚሆንበት ጊዜ መሳሪያው በራሱ ይጠፋል።

እርምጃ 4 - መዝጋት እና ማከማቻ

1 የ ON/OFF አዝራር በመጫን የ STREAM መሳሪያውን ያጥፉ።
2 በ STREAM መሳሪያ የሚመረተው ፀረ-ተባይ ሙመሙት በቀዝቃዛ/ጨለማ በታ ወደ ውስጥ በማያሰዩ ጠርሙሶች ውስጥ መቀመጥ አለበት።
* ፀረ-ተባይ አመንጭተው ከጨረሱ እና መሳሪያውን ለሌላ ጊዜ ለማስቀመጥ ዝግጁ ከሆኑ የሚከተሉትን ቅደም ተከተሎች ያጠናቅቁ።
3 ከትንሽ ቱቦ ውስጥ የጨው ሙመሙት ማጥለያውን በማላቀቅ በማጠራቀሚያ ቱቦ ውስጥ ያስቀምጡት። የትናንሽ ቱቦዎቹ ድጋፎች በትቦዎቹ ላይ መቆየታቸውን ያረጋግጡ። ክዳኑን በአስተማማኝ ሁኔታ በታው ላይ ይመልሱት እና በ STREAM ክዳን ውስጥ በሚገኘው ጥቁር ጥልፍ ከረጢት ውስጥ በ ያስቀምጡት።
4 ትንሹን እና ትልቁን ቱቦ በማያያዝ ዝግ ትቦ ይፍጠሩ።
5 ቱቦዎቹን እና የኤሌክትሪክ ገመዱን ወደ STREAM መያዣ ውስጥ በአስተማማኝ ሁኔታ በማስቀመጥ ይዝጉት።

እርምጃ 5 - መበረዝ

* የ STREAM መሳሪያው 5000 mg/L (0.5%) ክሎሪን በወጥ ፍሰት ያመርታል። የ STREAM ፀረ-ተባይ ሙመቱ ቅጥነት መጨረሻ ላይ በሚፈለገው የፀረ-ተባይ አጠቃቀም ላይ የተመሰረተ ነው።

| ዓላማ | የተወሰነ የውሃ መጠን ወደ 1 ሊትር ፀረ-ተባይ ውስጥ ይጨመራል | ውፍረት |
|---|---|---|
| **በከፍተኛ ደረጃ ለተበከሉ የጤና እንክብካቤ አካባቢዎች ጽዳት** | **0 ሊ** | **5000 ሚ.ግ/ሊ** |
| **እጅ መታጠብ እና የምግብ ዝግጅት** | **10 ሊ** | **5000 ሚ.ግ/ሊ** |
| **እጅ መታጠብ እና የምግብ ዝግጅት** | **2000 ሊ** | **2.5 ሚ.ግ/ሊ** |

እርምጃ 6 - ማጽዳት

* የካልሲየም ካርቦኔት ዝቃጭ በፍሳሽ ማስወገጃ ቱቦ ውስጥ በሚታይበት ጊዜ (ነጭ ንጥረ ነገር) ወይም ከፀረ-ተባይ ቱቦው ምንም ፍሳሽ እየወጣ አለመሆኑ ከተስተዋለ ማጽዳት ያስፈልጋል።
1 የማስወገጃ ቱቦው መጋጠሚያ ላይ ዝቃጭ (ነጭ ንጥረ ነገር) ተፈጥሮ ከሆነ ይመልከቱ።
2 ቱቦውን ይመልሱት እና የፍሳሽ ማስወገጃ ክፍሉን በአሲድ ወደማጠብ ይቀጥሉ።
3 0.5 ሊ (1 ፒን) አሴቲክ አሲድ ወይም ነጭ የተጣራ ኮምጣጤ በ 1 ሊትር የፕላስቲክ መያዣ ውስጥ ይጨምሩ።
4 ትንሹን ቱቦ ከጨው ሙመሙት ማጥለያው ጋር አሴቲክ አሲድ ወይም ኮምጣጤ የያዘው እቃ ውስጥ ያስቀምጡ።
5 ትልቁን ቱቦ - የፍሳሽ ማስወገጃ ቱቦ - ተመሳሳይ መያዣ ውስጥ ያስቀምጡ።
6 የ ON/OFF አዝራርን ተጭነው የስህተት ምልክት እስኪታይ ድረስ መሳሪያው እንዲሰራ ያድርጉ።
7 ON/OFF የሚለውን አዝራር በመጫን የ STREAM መሳሪያውን ያጥፉ።
8 ተመሳሳይ የኮምጣጤ ውህዱን በመጠቀም ይህን ሂደት 3 ጊዜ ይድገሙት።
9 እቃውን በ 0.5 ሊትር ንጹህ ውሃ ይሙሉ።
10 ትንሹን ቱቦ ከጨው ሙመሙት ማጥለያው ጋር 0.5 ሊትር ንጹህ ውሃው ውስጥ ያስገቡት።
11 የሚወገደውን ፈሳሽ ለመሰብሰብ ትልቁን የፍሳሽ ማስወገጃ ቱቦ በተለየ መያዣ ውስጥ ያስቀምጡት።
12 የ ON/OFF አዝራርን ተጭነው የስህተት ምልክት እስኪታይ ድረስ መሳሪያው እንዲሰራ ያድርጉ።
13 ቆሻሻ ፈሳሹን ያስወግዱ።
14 አሁን መሳሪያው ንጹህ እና ለአገልግሎት ወይም ለሌላ ጊዜ አገልግሎት ለመቀመጥ ዝግጁ ነው።

እርምጃ 7 - መፍትሔ መፈለጊያ መመሪያ

| ችግር | የማስተካከያ እርምጃ<br>(የ STREAM አሰራር መመሪያን ይመልከቱ) |
|---|---|
| **የመሳሪያው የኃይል ምንጭ መቋረጥ** | – የኃይል ምንጩን ይፈትሹ።<br>– መሳሪያው መሰካቱን ለማረጋገጥ የኃይል ገመዱን ይፈትሹ።<br>– ON/OFF አዝራሩን ይፈትሹ። |
| **የሚያንጠባጥቡ ቱቦዎች ወይም መጋጠሚያዎች** | – ኃይሉን ያጥፉ።<br>– የፍሳሹ መነሻ የቱ ጋር እንደሆነ ይለዩ።<br>– መጋጠሚያዎች ጥብቅ መሆናቸውን እና የትናንሽ ቱቦ ድጋፍ ማገናኛዎች አቅጣጫቸው ትክክል መሆናቸውን ያረጋግጡ። |
| **በመሳሪያው ውስጥ ምንም ፍሰት የለም** | – ማጥለያውን እና የትቦ መጋጠሚያውን ያጽዱ።<br>– በማጥለያ ወይም በትቦ ውስጥ መንጠባጠብ ካለ ይመርምሩ። |
| **ፓምፕ (ሞተር) አይሰራም** | – የቧንቧ መስመሮቹን ያጽዱ።<br>– ቱቦውን ከፓምፕ ማገናኛው ያላቅቁ። ንጹህ ውሃ በቱቦዎቹ ውስጥ ያፍስሱ።<br>– ቱቦውን ከፓምፕ ያላቅቁ እና ይወጥሩት። (በሚቀመጥበት ጊዜ ቱቦው ሊጠብቅ ይችላል።) |
| **የመሳሪያ ሙቀት መጨመር** | – ቱቦው ውስጥ ዝቃጭ ተፈጥሮ ከሆነ ይፈትሹ።<br>– መሳሪያውን ያጽዱ። |